# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# ዳዊት ንጉሱ
# (ክፍል 1)


ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጂ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ወጣቱ ዳዊት እየሮጠ ነበረ፡፡ ንጉስ ሳኦል ሊገድለው ፈልጓል፡፡ ዳዊት በምድርበዳ ነው የሚኖረው ፤ አራት መቶ ተከታዮች ባሉበት ትልቅ ዋሻ ውስጥ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፣ የንጉስ ሳኦል ወታደሮች ሊያገኙት ይቀርቡ ነበረ፡፡ ነገር ግን ዳዊት መሸሹን ይቀጥላል፡፡




የሳኦል አገልጋይ ዶይቅም ለንጉስ ዳዊት እንዲያመልጥ ፣ ካህናቱ እንዳገዙት ነገራቸው። ሳኦልም እነርሱ እንዲገደሉ ትዕዛዝን አወጣ። ነገር ግን ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ የነበረው ዶይቅ ብቻ ነበረ። እርሱም ጭካኔ በተሞላበት መልኩ ሰማንያ አምስት ካህናትን እና ቤተሰቦቻቸውን በሰይፍ ገደላቸው።
ይሄም እጅግ የከፋ ነበረ።
3


አንድ ቀን ፣ ሳኦል ዳዊትን እያሳደደው ባለበት ሰዓት ፣ ዳዊትና የእርሱ ሰዎች ወደሚደበቁበት ዋሻ አመረ ፤ ሳኦልም ብቻውን ነበረ።
4


በዋሻው ውስጥ ፣ ዳዊት ሳኦልን በቀላሉ ሊገድለው ይችል ነበረ። ነገር ግን ፣ ወደ እርሱ እጅግ ተጠግቶ በያዘው ስለት ልብሱን ቆርጦ ወሰደ።
ሳኦል ከሔደ በኋላ ፣ ዳዊት ወደ እርሱ ተጣራና ፣ “በዚህ ስለት የልብስህን ጫፍ ቆርጥኩት ፣ ነገር ግን አልገደልኩህም ፤ በእኔ ውስጥ ክፋትም ሆነ አመጽ አለመኖርን እወቅ።”
5


ሳኦልም ዳዊትን ሊጎዳው በመሞከሩ ተጸጸተ፤ ነገር ግን ፣ በፍጥነት ፣ የቆየው ንዴቱ መጣበትና ፣ ዳዊትን ለመግደል ሶስት ሺህ ሰራዊት አዘጋጀ። አንድ ምሽት ፣ ሰራዊቱ ሲተኛ ፣ ዳዊትና ከወታደሮቹ መካከል የሆነው አቢሳ አንድ ላይ የሳኦል ሰራዊት ወደሰፈረበትና ሳኦል ወደተኛበት ሰፈር ወረዱ።
6


አቢሳም እንዲህ አለ “በዚች ቀን እግዚአብሔር ጠላቶችህን በእጆችህ አሳልፎ ይሰጥሃል።” “እባክህን በያዝኩት ጦር አንድ ጊዜ ከመሬቱጋ ላጣብቀው ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ይሔንን አላደርገውም።”
7


ዳዊት ተቃወመው። የሳኦልን ጦርና ጋሻ ይዞት ፣ ሰፈሩን ለቀቀ። ከተራራው ጀምሮ በመንገዱ ሁሉ ፣ ሳኦል እስኪሰማው ድረስ ዳዊት ይጮህ ነበረ ፤ ነገር ግን አልሰማውም። አንዴ ለመጨረሻ ፣ ሳኦል ዳዊትን ሊጎዳው በመሞከሩ ሃዘን ተሰማው። ነገር ግን ዳዊት የሳኦልን ቃል ማመን አልቻለም።
8


በዚህም ሰዓት ሳሙኤል ሞቶ ነበረ፡፡ እርሱም ሳኦልን አስቀድሞ ፣ ከዚያም በማስከተል ዳዊትን የእስራኤል ንጉስ አድርጎ እንዲቀባው እግዚአብሔር የነገረው ነብይ ነው፡፡ ፍልስጤማዊያን እስራኤልን ሲያጠቁ ፣ ሳኦል አጅግ የሚያሳዝን ነገር አድርጎ ነበረ ፤ እግዚአብሔር የከለከለው አንድ ነገር፡፡
9


ከሙታን መካከል ሳሙኤልን እንድታስነሳለት አንዲትን ሴት ጠየቃት፡፡ ያን ምሽት ሳኦል አንድ መልዕክት አገኘ፡፡
10


እግዚአብሔር ከአንተ ተለይቶ ጠላትህ ሆኗል፡፡ መንግስትህን ወስዶት ለባልንጀራህ ለዳዊት ሰጥቶታል፡፡ ነገ፣ አንተ እና የአንተ ልጆች ከእኔጋ ይሆናሉ፡፡ አግዚአብሔር የእስራኤልን ሰራዊት ለፍልስጤማዊያን አሳልፎ ይሰጣቸዋል፡፡” ሳኦልም ይሄንን ሲሰማ ፣ በፍርሃት ራደ፡፡
11


ፍልስጤማዊያን ከእስራኤልጋ ተጣሉ ፤ የእስራኤል ሰዎችም ሸሹ፡፡ ፍልስጤማዊያን የሳኦልን ልጆች ፣ የዳዊትን ጥሩ ጓደኛ የሆነውን ዮናታንን ጨምሮ ገደሉ፡፡
12


ሳኦል በቀስተኞቹ ክፉኛ ተጎድቶ ነበረ፡፡ ለጦር አዝማቹ አንዲህ ይለው ነበረ “ጦርህን አውጣ እና ውጋኝ ፤ እነዚህ ክፉ ሰዎች መጥተው እኔን ከሚወጉኝ፡፡” ነገር ግን የጦር አበጋዙም እጅግ ፈርቶ ነበረና ፣ ሊያደርገው አልፈለገም፡፡” ስለዚህ ፣ ሳኦል ጎራዴውን ወሰደና ራሱ ወደቀበት፡፡
13


የሳኦልንና የልጆቹን አካል ካገኙ በኋላ ፣ በተያዙ የእስራኤል ግዛት ቅጥሮች ላይ ሰቀሉአቸው፡፡ አንዳንድ ጎበዝ እስራኤላዊያን አካላቱን ወደ ቤት ወስደው ከመቅበራቸው በፊት አቃጠሉት፡፡
14



ዳዊት ይሄንን እጅግ ዘግናኝ ዜና ከሰማ በኋላ ፣ በጎራዴ ወድቀዋልና ፣ ለሳኦል ፣ ለልጁም ለዮናታን ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በኀዘን እያለቀሰና ምግብ ሳይበላ እስከ ምሽት ሰዓት ድረስ ቆየ፡፡

15



ምንም እንኳን ሳኦል ዳዊትን ሊገድለው ቢሞክርም ፣ ዳዊት ሳኦልን እስከመጨረሻው ድረስ እግዚአብሔር እንደቀባው ያስብ ነበረ፡፡ አሁን እግዚአብሔር ዳዊትን አከበረው ፣ በሳኦል ቦታም ንጉስ አድርጎ ሾመው፡፡

16

ዳዊት ንጉሱ (ክፍል 1)

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

1ኛ ሳሙ 24-31፣ 2ኛ ሳሙኤል 1-2

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት 119:130**

17




20 60

18

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16

19